የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

ልሣነ- ሕግ ጋዜጣ

LISAN HIG GAZETA

OF THE BENISHANGUL — GUMUZ REGIONAL STATE

17 ኛ ዓመት ቁጥር 16 አሶሳ ታህሳስ 1991

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት

ም/ቤት ጠባቂነት የወጣ

17ተh Year No 16

Assosa Decmber 1999

ማ□·□

አዋጅ ቁጥር 16/1991 ፒ.ም

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልዊ መንግስት የሥራ አመራር ማሰልጠኛ ተቋም ማቋቋሚያ አዋጅ

CONTENTS

PROCLAMATION NO 16/1999

A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE BENISHANGUL GUMUZ NATIONAL REGIONAL STATE MILITIA

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር 16/1991 ዓ.ም**

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት □ሚሊሽያ ጽ/ቤት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የክልሉ ህዝብ ያስከበራቸውን ሕገ-መንግስታዊ መብቶችን: ጥቅሞችን: ሰላምና ደህንነቱን ለመጠበቅና ጥቅሞች በሀይልና በአመጽ ለመንጠቅ የሚመጡ ሀይሎች መመከትና መከላከል ይቻል ዘንድ የሕዝቡን የታጠቀ ሀጁል ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ:-

**Proclamation No 16, 1999**

A proclamation for Establishing the Militia Office of the Benishengul-Gumuz National Regional State.

WHEREAS, it has become necessary to organize a popular armed force for defending the constitutionally provided rights and well-being of the public against those who may use vid nce ro usurp same.

የቤኒሻንጉል /ጉሙዝ ብሄራዊ ክልል መንግስት አንቀጽ 47 (2) (ለ) መሠረት ከዚህ የሚከተለው ታውጇል::

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

**1. አጭር ርዕስ:**

ይህ አዋጅ « የቤኒሻንጉል / ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሚሊሺያ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 16/1991 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል»

**2. ትርጓሜ**

1. «ሚለሽያ» ማለት ከምርት ተ□ባሩ ላይ ሰነጠል በንግስት ወይም በግሉ በታጠቀው የጦር መሳሪያ ፀጥታ ለማስከበር በነዋሪው በነዋሪው በነዋሪው ህዝብ የተመረጠና ምንም አይነት የደመውዝ ክፊያ የማግኘት ታጣቂ ነው፡፡

2. «የሚሊሺየ ጽ/ቤት» ማለት በዚህ አዋጅ የተቋቋመውን ብሄራዊ መንግስት የሚሊሺያ ጽ/ቤት ነው::

**ክፍል ሁለት**

የሚሊሺያ ጽ/ቤት መቋቋም: ዓላማ: የጽ/ቤቱ ድርጅታዊ ተቋምና ተጠሪነት

NOW THERFORE, it is hereby proclaimed as follows in Accordance with Article 47 (2) (h) of the constitution of the Benishangul-Gumuz National Regional State.

PART ONE

**GENERAL**

**1. Short Title**

This proclamation may be cited as "Militia Office Establishing Proclamation No 16/1999, for Benishangul-Gumuz National Regional stat.

**2. Definition**

1. "Militia" means any popularly- elected resident who, without being given salary, may be deployed in protecting public security outside normal production activities.

2. "Militia office" Means militia office established in accordance with this proclamation.

**PART TWO**

Militia office Objectives, Organizational Structure and Accountability

**ምዕራፍ አንድ**
**ስለ የሚሊሽያ ጽ/ቤት መቋቋምና ዓላማ**

**3. ስለ ጽ/ቤቱ መቋቋም**

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሚሊሽያ ጽ/ቤት ከዚህ በኃላ «የሚሊሺያ ጽ/ቤት» እየተባለ የሚጠራ በ□ህ አዋጅ ተቋቋሞል፡፡

**4. የጽ/ቤቱ ዓላማ**

የሚሊሺያ ጽ/ቤት የሚከተለው ዓላማ ይኖረዋል::

በኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዲሚክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቤሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የተደነገጉ የሕዝቦችን መብቶችና ትቅሞች ሰላምና ደህንነት መጠበቅ እነዚህኑ በሀይል ለመንጠቅ ከሚደረጉ ሙከራዎች መካከል::

**ምዕራፍ ሁለት**

**የሚሊሺያ ጽ/ቤት ድርጅታዊ አቋምና ተጠሪነት**

5. የጽ/ቤት ድርጅታዊ አቋም

1. የሚሊሺያ ጽ/ቤት ክልላዊ፡ የዞንና የወረዳ አወቃቀር ይኖረዋል::

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ አንድ የተመለከተው እንደተጠበቀው ሆኖ ከወረዳ በታች በሚኖር የቀበሌና መሰል ዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች ተደራጅተውና ታጥቀው አገልግሎት የሚሰጡ የሚሊሺያ አባላት ይኖሩታል::

**CHAPTER ONE**

Objectives of Establishing Militia Office

3. Establishment of Office

The Militia office of the Benishangul –gumuz National Regional State hereafter called “Militia Office” is hereby established by this proclamation.

**4. Objectives of Office:**

The Militia Office shall have the following objective;

To protect the rights, interests, peace and security of peoples which are provided for in the laws of the FDERE and the Benishangul-Gumuz National Regional State against attempts by force; of usurp same

CHAPTER TWO

Organizational Structure and Accountability of Militia Office

5. **<u>Organizational Office Militia Structure</u>**

1. The militia office shall have regional, zonal and woreda structures

2. Without prejudice to the provision of sub-article one above the administrative set ups structured below the woreda hierarchy—at the kebele or

**6 ተጠሪነት**

1. ተጠሪነቱ ለክልሉ መንግሥት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሆነ የጽ/ቤቱ ኃላፊ፣

2. በዞንና በወርዳ ተጠሪነታቸው በየእርከኑ ለሚገኙ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሆነ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩበታል፡፡

**ክፍል ሶስት**

**የሚሊሺያ ጽ/ቤት፣ የኃላፊውና የሚሊሺያዉ ሥልጣንና ተግባር**

**ምዕራፍ አንድ**

**የሚሊሺያ ጽ/ቤት ሥልጣንና ተግባር**

**7. የጽ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር**

የቢንሻንጉል /ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሚሊሽያ ጽ/ቤት የሚከተሊት ተግባራት ይኖሩበታል፡፡

1 በየእርከኑ የሚገኙ የሚሊሺያ ጽ/ቤቶችን ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ይመራል፡፡

2. በክልሉ መንግሥት በሚወጣው መመሪያ መሠረት ለሚቋቋመው ሚሊሺያ የሰው ኃይል ይመለምላል፣ ያደራጃል፣ ያስታጥቃል፣ ያሰማራል፣ ብቃታቸውን ለማሳደግ የሚያስችል የግንባታ ሥራን በበላይነት ይመራል፡፡

**6. Accountability:**

The militia office shall have

1. Militia office head that is accountable to the executive committees of the regional state

2. Heads of zonal and woreda structures and staff members who are accountable to the executive committees of the various hierarchies

PART THREE

Powers and Duties of militia Office, Head and militia

**CHAPTER ONE**

Powers and Duties of Militia Office

7. Powers and Duties of Office

The militia office of the Benishangul-Gumuz National State shall have the following powers and duties

1. It shall organize, co-ordinate and direct militia office established at the various hierarchies.

2. It shall recruit, organize, arm and deploy the militia force to be established in accordance with directives to be issued by the regional state; it shall oversee militia mobilization and enhancement of their competence

Similar levels shall have militia members that are organized and armed

3. ለጽ/ቤቱ ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ያስተዳድራል፡፡

4. ወንጀል እንዳይፈጽም ይከታተላል፣ ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል ከሕዝባዊ ፖሊስ ጋር በመተባበር የአካባቢ የፀጥታ ሐይል ሆኖ ይሠራል፡፡

5. ሚሊሺያው ከምርት ተግባሩ ሳይነጠል በአካባቢው በሚካሄደው ፀጥታ የማስከበር እንቅስቃሴዎች ከሕዝባዊ ፖሊስና ከሕዝቡ ጋር የሠራበትን ሁኔታይፈጥራል፣ ይቆጣጠራል፣ ለረጅም ጊዜ ከምርት ሥራ የሚነጥል የፀጥታና ሌሎች መንግሥታዊ የረጅም ጊዜ ሥራዎች እንዲሠማራ ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፡፡

6. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሀገር ሠላምና ደህንነት ከሀገር መከላከያ ሠራዊት ጋር ይሠማራል፡፡

7. በሚወጣው ውስጠ ደንብ መሠረት አካሎችን ያስተዳድራል፡፡

8. እቅድና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

9. ሌሎች የሚሠጡትን ተግባራት ያከናዉናል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>የሚሊሺያ ጽ/ቤት ኃላፊ ስልጣንና</u> <u>ተግባር</u>

**8. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር**

3. It shall recruit and administer support-giving staff for the office

4. It shall work as a security force , in collaboration with public police, in monitoring , controlling and preventing against crimes .

5. It shall create conditions whereby the militia, without being away from production activities, may work in co-operation with public police in security protection activities, it shall monitor and oversee matters so that militiamen are not removed from production or governmental activities.

6. Where deemed necessary, it shall mobilize militia force for defense of public peace and security along with the national defense forces.

7. It shall administer its own organs in accordance with its own internal regulations.

8. It shall prepare and submit plans and budgets and work for execution of same.

9. It shall undertake such other duties are assigned to it.

## CHAPTER TWO

**8. Powers and Duties of militia Office Head**

የሚሊሺያ ጽ/ቤት ኃላፊ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ላይ ለሚሊሺያ ጽ/ቤት የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. ጽ/ቤቱን ይወክላል፣ ይመራል፣
2. የጽ/ቤቱን ዕቅድና በጀት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ሲፈቀድም በሥራ ላይ ይውላል፡፡
3. ጽ/ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከት በየሩብ አመቱ ሪፖርት ለቢኒሻንጉል/ ጉሙዝ ክልል ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሶስት</u>

## የሚሊሺያ ሥልጣንና ተግባር እና የሚሊሺያ አባልነትና ምልመላ

### 9. የሚሊሺያ ሥልጣንና ተግባር

**ማንኛውም የሚሊሺያ አባል ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡**

1. ወንጀል እንዳይፈጸም ይከታተላል፣ ይከላከላል፣ የሕብርተሰቡና ከህዝባዊ ፖሊስ ጋር በመተባበር የአካባቢዉን የፀጥታ ኃይል ሆኖ ይሠራል፡፡
2. ወንጀል ሲፈጽም ያገኘውን ሰው ይይዛል፣ ወዲያዉም ከኤግዚቢትነትና ከዝርዝር ሪፖርት ጋር በአቅራቢያው ለሚገኙ ፖሊስ ያስረክባል፡፡
3. የአካባቢዉ የአስተዳደርና የፍትህ አካላት የሚሠጡትን ተልዕኮዎች ይፈጽማል፡፡

While discharging the powers and duties assigned to the militia office in accordance with article 6 of this proclamation, the head of the militia office shall have the following powers and duties

1. He shall represent and direct the office
2. He shall cause the preparation of the plans and budget of the office; when approved, he shall execute same
3. He shall submit a quarterly report of the office's performance to the executive committee of the benishangul gumuz state

## <u>CHAPTER THREE</u>

**9. Power, duties, membership and recruitment of militia**

**Any militia shall have the following powers and duties**

1. He shall work as a security force, in collaboration with public police, in monitoring, controlling and preventing crimes.
2. He shall apprehend a person found committing offence he shall deliver the apprehended offender along with the exhibit and a detailed report.
3. He shall accomplish the duties assigned to the regional administration and justice bodies.

4. በሽፍትነት በስርቆት የተሰማራ እንዲሁም የወንጀል ድርጊት ለመፈጸም የተደራጀና ሕግ የሚጥሱ ሰዎች መኖራቸውን ሲገነዘብ በፍጥነት ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፡ የአካባቢውን ሕብረተሰብ በማስተባበር በቁጓ ጓ ር ሥር የሚውልበትን እርማጃ ይወስዳል፡፡

5. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሀገር ሰላምና ደህንነት ከሀገር መከላከያ ሠራዊት ጋር ይሠራል፡፡

6. ለረጅም ጊዜ ከምርት የሚነጠል የፀጥታና ሌሎች መንግስታዊ ሥራዎች ላይ ሊሰማራ አይፋባም፡ □መ□□ም □□ታ የለበትም፡፡

**10. የሚሊሺያ አባልነትና ምልመላ**

1. ማንኛውም ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ፡ ጤናማ አእምሮና አካላዊ ብቃት ያለው፡ የፆታ ልዩነት ሳይደረግ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ቀበለዎች ነዋር የሆነ ጥሩ የሥነ ምግባር ያለው ኢትዮጲያዊ የሚሊሺያ አባል ሊሆን ይችላል፡፡

2. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በፍቃደኝነት አባል የሆነ የሚሊሺያ አባል የመሰናበት መብት አለው፡፡

3. የሚሊሺያ አባ ምልመላ በአካባቢው ነዋሪዎች ቀዓ ተኛ ተሳትፎ የሚመረጥ ሲሆን የአፈጻጸሙ ዝርዝር ወደፊት በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

4. Where the delegates the existence of an organized group or people engaging in acts of bandit, theft or criminal offense, he shall take appropriate actions for their arrest by mobilizing the community members.

5. Where deemed necessary, he shall work in collaboration with the national defense force for protection of public peace and security.

6. He shall not be deploy in security or other governmental activities that may keep him away from production for a long time, he may not be obliged to engage in such activities.

**10. Militia Membership and Recruitment**

1. Any Ethiopian above 18 years of age who is in a good physical and mental health and with good conduct may, without any discrimination as to sex, become a militia member in the kebele of which he is resident.

2. Any militia who has been recruited as militia voluntarily shall have the right to be discharged.

3. Militia members shall be selected and recruited through direct participation of local residents and particulars shall be specified in regulations to be issued later on.

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 11. ስለ ትጥቅ ሕጋዊነት

1. በሚወጣው የሚሊሺያ መመሪያ መሠረት ተመልምሎ የሚታጠቅ የሚሊሺያ ሰራዊት አባል ሕፉዊ ታጣቂ መሆኑን የሚያረጋግጥ የመታወቂያ ደብተር ይኖረዋል።

2. ማንኛውም የሚሊሺያ አባል የሚይዘው ትጥቅ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ለተሰጠው ስልጣንና ተግባር ብቻ ጹፀለፀልበታል።

3. ማኝናውም ሚሊሺያ በመንግስት የተሰጠውን ትጥቅ መሸጥ፡ መለወጥ፡ ማዋስና አሳልፎ መስጠት፡ ማከራዬት፡ ማበላሸት በሕግ መሠረት ይቀጣል፡፡

### 12. ስለ ውስጥ ደንብ

ስለ ሚሊሺያ ምልመላ፡ ስልጠና፡ ስነ ምግባር፡ ስንብት በሚመለከት በክልሉ መንግስት ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጠ ደንብ ይወጣል።

### 13. በጀት

የጽ/ቤቱ በጀት በመንግስት ይመደባል።

### 14. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

በክልሉ ልሳነ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ያረጋል አይሸሽም ብርሃኔ

□ቤ/ቶ/ብ/□/መ/ ርዕስ መስተዳድር

አሶሳ

## PART FOUR

## Miscellaneous Provisions

### 11. Lawfulness of Arms Holding

1. Any militia member who is recruited according to militia directive shall hold an I.D card ascertaining that he is a lawfully armed person.

2. Any militia member shall use the arms he is holding for executing the powers and duties he is legally entrusted with.

3. Any militia member found engaging in selling, battering, lending, leasing or demanding the arms he is holding is punishable by law.

### 12. Internal Regulation

The Executive committee of the regional State shall issue an internal regulation concerning militia recruitment, training code of conduct and discharge.

### 13. Budget

The budget of the office shall be allocated by the government.

14. Effective date

This proclamation shall come into force as of the date of its publication in the state's Lisane-Hig Newspaper.

Ato Yargal Aisheshim Berhane

President of the Benishangul-Gumuz National Regional State

Assosa